# የኢትዮጵያዊ ነፃነቱ ስንት የኖርዌይ ዲናር ያወጣል!

(ሶሎሞን አ.)

እናቴ መቼስ የምትገርም እናት ናት!

የማይገርም እናት አለ እንዴ? ብሎ ለጠየቀ ሰው የምመልሰው መልስ “የለም” ይሆንና ነገር ግን ተፈጥሮ የለገሰቻቸውን የሚያስገርም እናትነታቸው ላይ አስተዳደጋቸው፣ አኗኗራቸው፣ ሃይማኖታቸው፣ ባሕላቸው ሲታከልበት ያንዷ እናት ባሕሪ ከሌላዋ መጠነኛ ልዩነት ይፈጥራል መሰለኝ የኔ እናት ትንሽ ትለያለች ከጎረቤት ካሉ እናቶች ጋር ስትነፃፀር። ይህን ደግሞ ብዙዎቹ የጎረቤት የእድሜ እኩዮቿም ይስማሙበታል። እናም ገና ጡት መጥባት ሳላቆም እናቴ ጥላኝ ወደ ገዳም ለንግስ ትሄዳለች። አንተን ይገፎ ፀሎቴ አይሰማልኝም ብላ ይሆን ወይም ለእግዚአብሄር የምትነግረውን ሚስጥር ከጀርባዋ ሆኜ እንዳልሰማት፤ እስካሁን ባላወቅኩት ምክንያት ጎረቤታችን ላሉ አሮጊት ጥላኝ ከቢጤዎቿ ጋር “እሰይ ስለቴ ሰመረ” እያለች ሔደች።

ልጅ ሲርበው ያለቅሳል፤ ራበኝ ማለት እስኪችል፤ ርኃቡን በቋንቋ መግለፅ እስኪጀምር ድረስ። ለነገሩ የሚያለቅስባቸው ምክንያቶች ብዙ ብዙ ናቸው። አሁን ግን እያወራሁ ያለሁት ስለኔ ለቅሶ ነው። ያን ቀን አለቀስኩ አሉ። የተነፋረቅኩበትን ምክንያትም እናቴ ናፍቃኝ እንዳልሆነ አሮጊቷ አስወሩ፣ ርቦኝ ብቻ እንዳላለቀስኩ ልቦናቸው እያወቀ። ሆዴ ጎደል ሲል ነው አሉ ንጭንጭ የጀመርኩት ከዚያም አፌን መክፈት ስጀምር በርራሳቸ ቋንቋ ማባባል ይጀምራሉ አደራ የተባሉት የጎረቤት አሮጊት። እየተውረገረገች አደራ ብላቸው ስለሄደች በእንክብካቤ ለመያዝ ጥረት እያደረጉ ነው እንዳልል እናቴ መውረግረግ አትችልበትም እሳቸውም ለኔ ግድ አይሰጣቸውም። መውረግረግ ብትሞክር እንኳ ውለታ እየጠየቀች መውረግረግን ምን አመጣው? ወደ ቤተ እግዚአብሄር እየተሄደስ መውረግረግ ምን ይሚሉት ፈሊጥ ነው? ስለዚህ በርግጠኝነት ለመናገር የምችለው ትሁቷ እናቴ በትህትና አደራ ብላቸዋለች።

እሳቸውም አደራቸውን ለመወጣት ደፋ ቀና ሲሉ ከሚያደጉልኝ ነገሮች ውስጥ አንዳቸውም አልጣሙኝም አሉ። ስለዚህ ለቅሶዬን ቀጠልኩ። ግራ ሲገባቸው ሊያታልሉኝ ይሞክራሉ። እናት ሆነው ያሳደጓቸው ብዙ የጉድ ልጆች ነበራቸው። ስለዚህ እንደ እናት ማቀፍ አያቅታቸውምና አቀፉኝ። ሲያቅፉኝም እኔ ለቅሶዬን አላቋረጥኩም። ቀጠሉና ጡታቸውን አጎረሱኝ። ያኔ ፀጥ አልኩ አሉ ደክሞኝና እርቦኝ ስለነበር። ያን ቀን ታዲያ የጎረስኩትን ጡት እየጠባሁ እንደወትሮው አልሆንኩም፣ ጡት አገኘሁ ብዬ ስመጠምጥ ከቆየሁ ቡኃላ ጡቱ ሲደርቅብኝ መጀመሪያ ጡቱን ከአፌ አላቅቄ ሁለት ነገሮችን ፈፀምኩ። አንደኛው “ምናባኩ” የሚል ስድብ ቃል አወጣሁ፤ ቀጠልኩና ደረቁን ጡታቸውን በትንሽ መዳፌ በጥፊ ነረትኩላቸው። “ምናባኩ” ብዬ ስሣደብ ምናልባት ጡታቸው መድረቁ አናዶኝ ሊሆን ይችላል። በጥፊ ስመርግላቸው ግን  ከንዴት ያለፈ ብሶት፣ ተስፋ መቁረጥ፣ የፍቅር ማጣት፣ ብቸኝነት፣ ናፍቆት እና ቁጭት በውስጤ ስለተፈጠረ ነው አሉ። ይህ የሁለት ቀን የልጅነት ታሪኬ ነው።

በጉብዝናዬ ወራት ደግሞ ታሪክ ራሱን ይደግማል ሆነና የልጅነቷን ባላደራ የጎረቤት አሮጊት ምናቸውም ሳይቀየር አገሬ ሆነው መጡብኝ። አድጌ ደግሞ የደረቀ ጡት እያጠባ የሚያላግጥብኝ ወያኔ ሆኖ አገኘሁት። በደረቅ ዴሞክራሲ፣ በደረቅ ፍትሕ፣ በደረቅ ነፃነት ቢፈታተነኝ ተቆጣሁና ከማይሸነፈው ጋር ታገልኩ። ወያኔ በሕገመንግስቱ ማንኛውም ሰው ያለማንም ጣልቃ ገብነት የመሰለውን አመለካከት ለመያዝ ይችላል ቢልም እንዳሮጊቷ ጡት ደረቅ፣ የቃላት ክምር ከመከመር ያለፈ ፋይዳ ያለው ነገር ሊወጣው አልቻለም። ስለሆነም በአመለካከቴ ተናቅኩ ተገፋሁ፣ መሰረታዊ መብቶቼና የነፃነት እውቀቶቼ ሙሉ በሙሉ ተገደቡ፤ ሕገመንግስቱ ደህንነቴን ሊያስጠብቅልኝ አልቻለም ስለዚህ ለሕይወቴ ፈራሁ፣ አገሬን ጥዬ እግሬ ወዳመራኝ ተሰደድኩ። በዘመድና በጓደኛ ድጋፍ ዞሬ ዞሬ ኖርዌይ ደርሼ አዲስ የስደት ታሪክ ለነገ እየፃፍኩ እገኛለሁ። ታሪክ የሚሰራው ለነገ ስለሆነ።

እናታቸው አገራቸው የሆነችላቸው፣ እናታቸው ጥላቸው ያልሔደችባቸው፣ እናታቸው የምትንከባከባቸው ኖርዌጅያን ደስተኛ ባይመስሉም የተረጋጉና ሰላማዊ ሕዝቦች ናቸው። ባለስልጣናቱ ደግሞ አገራችን የጎረቤት አሮጊት የሆነችብን በብሶት፣ በተስፋ መቁረጥ፣ በርኃብ፣ በድኅነትና ክፋት ጥለናት እንድንሰደድ የተገደድን ኢትዮጵያውያን ላይ በሚከተሉት የተሳሳተ ፖሊሲ ምክንያት የተጻፈ የማያነቡ፣ ቢያነቡም ለመረዳት የማይፈልጉ፤ የተነገረ የማይሰሙ፣ ቢሰሙም የማይጨነቁ፤ የተጠየቁትን የማያዳምጡ ቢያዳምጡም የማይመልሱ ከሆኑ አመታት ተቆጠሩ። ኬዝን በመልክ በመልኩ ከማየት ይልቅ በጅምላ ፍረጃቸው ከዚህ መልስ ፖዘቲቭ የተቀረው ኔጌቲቭ እያሉ አገራቸውን በእድል የሚኖርባት አገር አደረጓት። የጥገኝነት ትርጉሙ እስኪጠፋብን ድረስ አደናግረውን የሚሆነውን ስንጠብቅ ዛሬ ለአምባገነኑ መለስ አሳልፈው ሊሰጡን መስማማታቸውን አበሰሩን። ባላቸው የተፅእኖን የመፍጠር ፍላጎትና የጣልቃገብነት የውጭ ፖሊሲ ምክንያት በአገራችን ያለውን የሰብዓዊ መብት ጥሰት እንዳላዩ በማለፍ ከመለስ መንግስት ጋራ ሲሞዳሞዱ ኖረው አሁን የወያኔን መንግስት ሸሽቶ ጥገኝነት የጠየቀን ስደተኛ ወደኢትዮጵያ ምድር ለመመለስ ከመለስ መንግስት ጋር ስምምነት ተፈራረሙ።

አሁን አገሪቱን እያስተዳደረ ያለው የሰራተኛ ማሕበሩ ፓርቲ በሚቀጥለው አመት የሚከናወነውን ምርጫ ድምፅ ለማሰባሰብና ከዋንኛው ተቀናቃኙ ልቆ ለመታየት በስደተኛ ላይ ያለው አቋሙ ወሳኝ እንደሆነና ይሕንንም በኢትዮጵያውያን ላይ ሲተገብር እንደ ትልቅ ድል እንደሚቆጠርለት ይነገራል። እንዲሁም ይሕ ስምምነት የወያኔ መንግስት በዜጎች ላይ በጨከነበት፣ የከፋ አፋኝ በሆነበት በአሁኑ ሰዓት መደረጉ ከአመት በፊት የርኃብ አድማ በመቱ ኢትዮጵያውያንና በኖርዌይ መንግስት መካከል ተፈጥሮ በነበረው የከረረ ውዝግብ እልሕ ተጋብቶ የነበረው ይህ መንግስት ያንን ውዝግብ ባሸናፊነት ተወጣሁት ለማለት የተደረገ ስምምነት አስመስሎታል።

በጥር 2003 ዓም እስከ 17 አመት በኖርዌይ ውስጥ ቤተሰብ መስርተው፣ ኃብት ንብረት አፍርተው፣ ግብር እየከፈሉ ከኖርዌጅያን ማሕበረሰብ ጋር በሰላም ይኖሩ የነበሩትን ኢትዮጵያውያን ከአገር እንዲወጡ ሲያስገድዷቸው ለክፉ ቀን መጠጊያ ወደሆነው ወደ እግዚያብሔር ቤት ያመሩና እዛ ይጠጋሉ። በወቅቱ ታዲያ በዚያ ክረምት፣ በዚያ በሚያቃጥል ብርድና ቁር ሕፃናትና እመጫቶች ሲሰቃዩ ገሎ እንደሚሸልል ጀግና በኢትዮጵያውያኑ ላይ ይባል የነበረውን ነገር እዚህ ላይ መፃፍ ተገቢ ስላልሆነና ስለሚያስቆጭ አልፈዋለሁ። ነገር ግን በወቅቱ ሕፃናትና ሴቶች ከኢትዮጵያ ሲሆኑ ዋጋቸው ለኖዌጅያን ስንት እንደሆነ አይተናል፣ የሰብዓዊነት ልካቸውንም ታዝበናል።

ሳንሰደድም በመንግስት እንደዜጋ አልተከበርንም፣ ሳንሰደድ ሕገመንግስቱ ደህንነታችን አላስጠበቀልንም፣ የነፃነት መንገዶችን ሁሉ ሲዘጉብን አገር ጥለን ተሰደድን የምንል እኛ በዚህ አገር የምንኖር ስደተኞች ለነፃነት የምንታገለው ከመለስ ጋር ብቻ ሳይሆን ከኖርዌይ መንግስት ጋርም ነበር። በወያኔ የሃያ አመት የስልጣን ቆይታ የገዢውን ሃሳብ ተቃውሞ ያልተዘለፈ ያልታሰረ ተቃዋሚ አለ? የአቶ መለስን አካሄድ ነቅፎ ያልታሰረ ተቀናቃኝ አለ? መንግስትን ኢ-ፍትሃዊነት ፅፎ ያልታሰረ ጋዜጠኛ አለ።  አቢዮታዊ ዲሞክራሲን፣ የገጠር ልማት ስትራቴጂን፣ የመሬት ፖሊሲን … መዝኖ "ፖሊሲዎ ቀሎ ተገኝ" ብሎ በአቶ መለስ አንደበት ያልተሰደበ አገርኛ ምሁር ወይም ባይተዋር ፈረንጅ አለ? እያልን ብንጮህም የሚሰማ ጆሮ አጣን ስለሆነም አይናችን እያየ ወደ መለስ ልንወረወርና የመውጊያውን ብረት እንድንረግጥ ልንገደድ ሆነ።

ይህን የመውጊያ ብረት ለመርገጥ ወይም ቂም የያዘችዋን የጎረቤት አሮጊት ለመጋፈጥ ባስቀመጡት ቀነገደብ ውስጥ ለመጣ ስደተኛ ተዝቆ ከማያልቀው ንዋያቸው ሊቆነጥሩልን ቃል የገቡት ባለስልጣናቱ የኢትዮጵያዊ ዋጋው አንድ ወር አገራቸው ላይ መስራት ብቻ እንደሆነ በጨረፍታ ነግረውናል። እስከ ማርች 15 2012 ተላልፎ ሊሰጥ የፈቀደ የአንድ አነግ፣ የአንድ ግንቦት 7፣ የአንድ ኦብነግ፣ የአንድ ኢሕአፓ፣ የአንድ የሰብዓዊ መብት ተሟጋች ኢትዮጵያዊ የነፃነቱ፣ የክብሩ፣ የሰውነቱ ዋጋው 45 ሺ የኖርዌይ ዲናር እንደሆነ በነጋሪት ተጎስሞ ሰምተናል። እስከዚህች የምፅአት ቀን ጽዋውን ለመጎንጨት ያመነታ ዋጋው ከዋናው ወደ ሲሶ ይወርዳል፣ እንደጆሌ ይቆጠራል፣ በፖሊስ ይታደናል፣ እጁን ወደኋላ ታስሮ በውርደት ለመለስ ተላልፎ የሰጣል። ይህ ማለት እንደገና ስደት ወደ ኢትዮጵያ፣ ግዞት ወደራስ አገር ታውጆብናል ማለት ነው።
ይህ ሁሉ ሲሆን በዲያስፓራው ውስጥ ጠንካራ የሚባሉት ተቃዋሚ ፓርቲዎች እንዴት ነው ድምፃቸውን ማሰማት የከበዳቸው? አሰምተዋል እንኳን ብንል የት ድረስ ተሰምተዋል? አንዳንዶች በአውሮፓውያን ፓርላማ ላይ ንግግር ሲያደረጉ አይተናል፣ ለምን እዚህኛው አገር ላይ ተፅእኖ ምፍጠር አልፈለጉም? ለደጋፊዎቻቸው ጥብቅና መቆም ቢያቅታቸው ለምንድነው በወያኔ እጅ ለሚገቡት አባላቶቻቸውና ስለሚባክነው ሚስጥራቸው ያልተጨነቁት? ለምንድነው ድምፃቸውን ለወገናቸው ማሰማት የከበዳቸው? ለሰብዓዊ መብት ቆመናል የሚሉትና አለምዓቀፍ ድጋፍ እንዳላቸው የሚነገርላቸው ድርጅቶች የኢትዮጵያውያኑ ሕይወትና ነፃነት በፖለቲካ አመለካከታቸው ምክንያት፣ በፓርቲ አባልነታቸው ምክንያት፣ በዘራቸው ምክንያት አደጋ ላይ ሲወድቅ እንዴት መከራከር ተሳናቸው።

እስቲ ይታያችሁ ይህ ሁሉ ኢትዮጵያዊ በጉልበት ከተመለሰ ቡኃላ ስንትና ስንት ክፍል ያለው አኬልዳማ ድራማ በኢቲቪ እንደሚሰራ። እስቲ አስቡት እያንዳንዱ ከስደት ተመላሽ በእነ በረከት ተደርሶ የሚሰጠውን ልማታዊ ተውኔት እንዲተውን፣ ልማታዊ ቃለ-መጠይቅ እንዲሰጥ ሲገደድና በስንት ልማታዊ ልዩ ዝግጅት ላይ እንዲናዘዝ ሲደረግ። በኖርዌይ ምድር ላይ በስደተኛ ወገኖቻችን ላይ እየሆነ ያለውን ነገር ማሰብ ከቻልን? ከሆነ ቡኃላ መፈክር ይዞ በየጎዳናው በብርድና በቁር ከመቃጠል፣ ፍሪ … ስቶፕ ሰፖርቲንግ … እያሉ የቁራ ጩኸት ከመጮህ አሁኑኑ ድምጻችንን ባንድነት ብናሰማ መልካም ነበር …።

ሶሎሞን አ.
**negasi08@gmail.com**